- የጤና ባለሙያዎች የፀረ-ተህዋስያን መድኃኒቶችን አለአግባብ እንዲያዙ መገፋፋት

- የፀረ-ተህዋስያን ቅሪት ያለበትን የእንስሳት ተዋፅኦ መመገብ

- ጥቅም ላይ ያልዋሉ የፀረ-ተህወስያን መድኃኒቶች ያለአግባብ በቆሻሻ መልክ መጣል

## 2. የፀረ-ተህዋስያን መድኃኒቶች በጀርሞች መለመድ የሚያስከትለው ችግር ምንድነው?

- በሽታ አምጪ ተህዋስያን
በቀላሉ በመድኃኒት መወገድ ባለመቻላቸው ምክንያት ህሙማን ለተጨማሪ ህመምና ወጪ እንዲሁም እንግልት ይዳርጋሉ፤

- በቁጥር ውስን የሆኑት እነዚህ የጸረ ተህዋስያን መድሃኒቶች ከአገልግሎት ውጪ ይሆናሉ፤

- የጎንዮሽ ጉዳታቸው ከፍ ያለ መድኃኒቶችን ለመውሰድ እንገደዳለን፤

- በተመላላሽ ህክምናመታከም የሚችሉ ህመሞችን ሆስፒታል ተኝቶ መታከም ሊኖርብን ይችላል፤

- ከፀረ-ተህዋስያን መድኃኒቶች ጋር የተላመዱ በሽታ አምጪ ጀርሞች ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው ስለሚተላለፍ የህብረተሰብ ችግር ይሆናል፤

- ምርታማነት ይቀንሳል፣ በግለሰብና በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ችግር ያስከትላል

- በመጨረሻም በገበያ ላይ ያሉ መድኃኒቶች በሽታ አምጪ ጀርሞችን ማከም ባለመቻላቸው ለሞት ይዳርጋሉ።

## 3. ፀረ-ተህዋስያን መድኃኒቶች በጀርሞች መለመድን እንዴት መከላከል ይቻላል?

- መድኃኒቶችን በጤና ባለሙያ ትዕዛዝ መሰረት ብቻ በመውሰድ፤

- ለሌላ ሰው የታዘዘን መድኃኒት ባለመዋዋስ/ ባለመጠቀም፤

- በቂ የሆነ ምርምራ በማድረግ የህመሙን አይነትና ደረጃ በማወቅ መድኃኒቶችን በመውሰድ ፤

- የግልና የአካባቢን ንጽህና በመጠበቅ፤

- ምግቦችን በሚገባ አጥቦ በማብሰል መመገብ

- ለአንዳንድ የጸረ-ተህዋስያን መድኃኒቶች አለርጂ ከሆንን መድኃኒት በሚታዘዝልን ወቅት በቅድሚያ ለባለሙያው በመናገር፤

- ለተወሰነ ቀን የፀረ-ተህዋስያን መድኃኒቶችን ወስደን ቢሻለን እንኳን መድኃኒቱን እስከመጨረሻው ቀን ድረስ በመውሰድ

- የፀረ-ተህዋስያን መድኃኒቶችን ከታዘዘው መጠን አሳንሶ ወይም አብልጦ ባለመጠቀም

- የፀረ-ተዋስያን መድኃኒቶች ታዝዘው መውሰድ ከተጀመረ በኋላ የጤና ባለሙያ ሳያማክሩ ባለማቋረጥ

- አግባብ ያልሆነ የጸረ-ተዋስያን መድኃኒቶች አጠቃቀም ለእርስዎ፣ ለልጅዎ፣ ለቤተሰቦ እና ለህብረተሰቡ ጎጂ መሆኑን በመገንዘብ

- ከፀረ-ተህዋስያን መድኃኒቶች ጋር የተላመዱ በሽታ አምጭ ጀርሞች ሲያጋጥም በቶሎ ምርመራ ማድረግ

- የፀረ-ተህዋስያን መድኃኒቶችን ለሰውና ለእንስሳት በአግባቡ በመጠቀም

- ደህንነታቸው፣ፈዋሽነታቸው እና ጥራታቸው የተረጋገጠ መድኃኒቶች ህጋዊ ከሆኑ መድኃኒት ቤቶች መግዛት

Supported by fraycollege , September 25

fraycollege
Of Communications

# የፀረ-ተህዋስያን መድኃኒቶች ፍቱንነት እጣ ፋንታ በሁላችን እጅ ላይ ነው!!



# የፀረ-ተህዋስያን መድኃኒቶች በበሽታ አምጪ ጀርሞች መለመድ የሚያስከትለው ችግርና መከላከያ መንገዶች

የፀረ-ተህዋስያን መድኃኒቶች በበሽታ አምጪ ተህዋስያን አማካኝነት በሰውና በእንስሳት ላይ የሚደርስ ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከልና ለማከም የምንጠቀማቸው መድኃኒቶች ሲሆኑ እነዚህ መድኃኒቶች በአይነት፣ በይዘታቸውና በአጠቃቀማቸው የተለያዩ ናቸው።

የፀረ-ተህዋስያን መድኃኒቶች ከዛሬ 80 ዓመት በፊት መፈልሰፍ ለሰው ልጆች ጤና ከፍተኛ እፎይታን በመስጠት አለም ከደረሰባቸው ትልልቅ የሳይንስ ውጤቶች ውስጥ እጅግ ጠቃሚ በመሆን የሰው ልጆችና እንስሳት ከሚደርስባቸው ስቃይና ሞት መታደግ ችሏል።

በኢትዮጵያ አብዛኞቹ በሽታዎች ተላላፊ ሲሆኑ እነዚህን ለማከምና ለመከላከል የፀ-ተህዋስያን መድኃኒቶች ቁልፍ ሚናን ይጫወታሉ። የፀረ-ተህዋስያን መድኃኒቶች በከፍተኛ ደረጃ ተላላፊ በሽታዎችን መከላከልና ማከም በመቻላቸው ምክንያት በስፋት እና በአብዛኛው አግባብ ባልሆነ ሁኔታ ጥቅም ላይ እንዲውሉ አድርጓቸዋል።

አግባብ ያልሆነ የፀረ-ተህዋስያን መድኃኒቶች አጠቃቀም ደግሞ መድኃኒቶች በበሽታ አምጪ ተህዋስያን በቀላሉ እንዲለመዱ ያደርጋቸዋል።

የፀረ-ተህዋስያን መድኃኒቶች በጀርሞች መለመድ ማለት በተህዋስያን አማካኝነት ለሚመጣ ህመም የሚወሰዱ መድኃኒቶች ተህዋስያንንመግደል፣ መቆጣጠር ወይም መራባታቸውን መግታት ሲሳናቸው ሲሆን በዚህ ጊዜ መድኃኒቶች በደም ውስጥ ቢኖሩም ተህዋስያኑ መራባት ይችላሉ ማለት ነው።

የጸረ-ተህዋስያን መድኃኒቶች በጀርሞች መለመድ አለማችን ከሚያሰጓት ትልልቅ ችግሮች መካከል የሚጠቀስ ሲሆን በሰው በእንስሳትና በአካባቢ ጤና እንዲሁም በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ችግር እያስከተለ ይገኛል። ይህ ችግር በሁሉም የአለም ክፍል የሚታይ ቢሆንም እንደ ሃገራችን ባሉ ታዳጊ አገራት የችግሩ አሳሳቢነት ጎልቶ ይታያል። የችግሩን አሳሳቢነት በጥቂቱ ለመጠቆም ያህል የቲቢ፣ ኤች.አይ.ቪ እና የወባ መድኃኒቶች እንደዚሁም በስፋት በምንጠቀምባቸው በሌሎች የጸረ- ተህዋስያን መድሃኒቶች ላይ እየተከሰተ ያለው በጀርሞች መለመድ ችግር ግልጽ ማሳያ ነው። ይህ ችግር በእንስሳት ጤና ላይም በስፋት ጎልቶ ይታያል።

አንዳንድ የጥናት ውጤቶች እንደሚያመላክቱት በዚህ ችግር ምክንያት በዓለም ላይ ከ700ሺህ በላይ የሚሆኑ ሰዎች በየአመቱ የሚሞቱ ሲሆን ችግሩን ለመቀነስ እርምጃ ካልተወሰደ እ.ኤ.አ በ2050 ወደ 10 ሚሊየን የሚጠጉ ሰዎች ይሞታሉ ተብሎ ይገመታል። ችግሩ ከዚህም ባለፈ በአጠቃላይ የዓለም ኢኮኖሚ ላይ ከ2 እስከ 3% ማለትም ወደ 10ትሪሊየን ዶላር ኪሳራ እንደሚያሰከትል ይገመታል። በታዳጊ አገሮችም ከ5% በላይ የኢኮኖሚ ኪሳራ እንደሚያደርስ ይታመናል።

ይህንን አለምአቀፍ ችግር ለመግታትና ለመቆጣጠር የአለም ጤና ድርጅት፤ የአለም የምግብና ግብርና ድርጅት እና የአለም የእንስሳት ጤና ድርጅት በመተባበር አለም አቀፍ የጸረ ተህዋሲያን መድሃኒት መለመድ የመከላከልና የመቆጣጠር ስትራተጂና ዕቅድ አውጥተው አባል አገሮች ተግባራዊ እንዲያደርጉ ጥረት በማድረግ ላይ ናቸው። አገራችን ኢትዮጵያም የጸረ ተህዋስያን መድሃኒቶች መለመድ በሰው፤ በእንስሳትና አካባቢ ጤና እንዲሁም በኢኮኖሚ ላይ እያደረሰ ያለውን ችግር በመገንዘብ ስትራቴጂክ እቅድ በማውጣትና ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ሙያተኞችን ያካተተ አገራዊ አማካሪ ኮሚቴ በማዋቀር ላለፉት አስር አመታት የጸረተህሳዋያን መድሃኒቶች መለመድን የመከላከልና የመቆጣጠር ስራዎች በሰው፤ በእንሰሳትና በአከባባ ጤና ዘርፍ በርካታ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ።

ስለሆነም ችግሩን መከላከልና መቆጣጠር ለአንድ አካል ብቻ ሀላፊነት ሰጥተን የምንተወው ጉዳይ ሳይሆን መላው ህብረተሰብ፣ የሃይማኖት መሪዎች፤ የሲቪክ ማህበራት፤ የሰው፤ የእንስሳትና የአካባበቢ ጤና ባለሙያዎች፣ የጤና ቁጥጥር አካላት፣ ፖሊሲ አውጪዎች፣መገናኛ ብዙሀንና ሌሎች መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በጋራ በመሆን ሃላፊነታችንን መወጣት ይኖርብናል።

## 1. ለፀረ-ተህዋስያን መድኃኒቶች በጀርሞች መለመድ ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

የፀረ-ተህዋስያን መድሃኒቶች በጀርሞች መለመድ በተለያዩ ምክንያቶች ሊከሰት ይችላል። እነዚህም፡-

- የፀረ-ተህዋስያን መድኃኒቶችን ያለ ጤና ባለሙያ ትዕዛዝ መውሰድ
- የታዘዘን የፀረ-ተህዋስያን መድኃኒቶች ማቋረጥ፤
- የታዘዘን መድኃኒት መጠን በመቀነስና በመጨመር መውሰድ፤
- የፀረ-ተህዋስያን መድኃኒቶችን ከሌላ ሰው ተውሶ መውሰድ፤
- የታዘዘን መድኃኒት መውሰጃ ሰዓት በማዛባት መውሰድ፤
- የጸረ-ተህዋስያን መድኃኒቶችን ለእንስሳት ያለ እንስሳት ህክምና ባለሙያ ትዕዛዝ መስጠት፤
- ከዚህ በፊት ተወስዶ ስላዳነ ብቻ ተመሳሳይ መድኃኒቶችን ገዝቶ መጠቀም፤
- መድኃኒት ለማያስፈልጋቸው ወይም ሰውነታችን በተፈጥሮ ባለው ሃይል ሊቋቋማቸው ለሚችሉ ህመሞች መድኃኒት መውሰድ፤
- የግልና የአካባቢ ንጽህናን አለመጠበቅ፤
- ትክክለኛ መድኃኒት ለትክክለኛው ህመም አለመውሰድ፤
- ትክክለኛ የመፈወስ አቅም የሌላቸውን መድኃኒቶች ህጋዊ ካልሆኑ መድኃኒት ቤቶች ወይም ግለሰቦች ገዝቶ መውሰድ፤

fraycollege
Of Communications